የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS


14 የካቲት 2009

ቀን.....
Date
ቁጥር መ6.2166/09
No.

**ለሁሉም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲዎች፣ ቋሚ መልእክተኛ ፣ ቆንስላ ጄኔራል፣ ንግድ ጽ/ቤቶች**

**<u>በያሉበት</u>**

**ጉዳዩ፡- <u>አምስት አመት የሞላቸው ቦንዶች የሚመለሱበት አግባብን በተመለከተ፤</u>**

በ2004 ዓ.ም. ቦንድ የገዙ የዳያስፖራ አባላት ገንዘባቸው የሚመለስበት ጊዜ በመድረሱ እንዲመለስላቸው እየጠየቁ እንደሚገኙ በመግለጽ ይህ ጥያቄ በምን መልኩ እንደሚስተናገድ ከአንዳንድ ሚስዮኖች ጥያቄ በመቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

አምስት አመት የሞላቸው ቦንድ የገዙ ደንበኞች ገንዘባቸው የሚመለስበትን አግባብ በተመለከተ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ባገኘነው መረጃ መሰረት የቦንድ ገዢዎች ገንዘብ የሚመለሰው በአካል ወይም በህጋዊ ወኪል የቦንድ ሰርተፍኬታቸውን ይዘው በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል መቅረብ ሲችሉ ነው፡፡ ነገር ግን ገንዘባቸውን በጥሬ ገንዘብ መውሰድ የሚፈልጉ ከሆነ የሚከፈላቸው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በእለቱ የምንዛሪ መጠን በአገር ውስጥ መገበያያ በሆነው ብር ሲሆን፣ በአገር ውስጥ የዳያስፖራ የውጭ ምንዛሪ አካውንት ወይም በውጭ አገር አካውንት ካላቸው ገንዘባቸው በውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚደረግላቸው ይሆናል፡፡

በዚሁ መሰረት በአሁን ወቅት የዳያስፖራ አባላት ቦንድ የገዙበት ገንዘብ እንዲመለስላቸው ለሚያቀርቡት ጥያቄ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል በአካል በመቅረብ እየተስተናገዱ ይገኛሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በውጭ አገር የሚኖሩ የዳያስፖራ አባላት ገንዘባቸው እንዲመለስላቸው ጥያቄ ሲያቀርቡ በህጋዊ ወኪሎቻቸው አማካኝነት የቦንድ ሰርተፍኬታቸውን በመላክ ገንዘባቸውን መውሰድ የሚችሉ ሲሆን፣ ወደ ባንክ አካውንት ገቢ እንዲደረግ የሚፈልጉ ከሆነ የባንክ አካውንታቸውን በሚስዮኖች አማካኝነት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማስተላለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዳያስፖራ አባላቱ የሚያቀርቡት ህጋዊ ውክልና ለዚሁ አገልግሎት እንደሚውል የሚጠቅስ መሆን ይኖርበታል፡፡

በመሆኑም ይህንን መረጃ በአግባቡ ቦንድ ለገዙ የዳያስፖራ አባላት እንድታሳውቁ እየጠየቅን፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ቦንድ የገዙ ደንበኞችን ገንዘብ ለመመለስም ሆነ የሚቀርቡ የወለድ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የተሟላ የቦንድ ገዥዎች መረጃ እንደሚያስፈልግ በመገንዘብ ከዚህ ቀደም በሚስዮኖቻችሁ ከተከናወኑ የቦንድ ሽያጮች መካከል ያልተላኩ መረጃዎች ካሉ በማጣራት እንድትልኩ እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ደመቀ አጥናፉ
ዳይሬክተር ጄኔራል
የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች
ዳይሬክቶሬት ጄኔራል

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር ሚኒስትር ዲኤታዎች ጽ/ቤት
- ለሁሉም አህጉራዊ ዳይሬክቶሬት ጄኔራሎች
  ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  <u>አዲስ አበባ</u>


ፋክስ ቁጥር
Fax 011-5-51 43 00
✉393 ☎011-5 51 73 45 E-mail:mfa.addis@telecom.net.et
አዲስ አበባ:- ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia